የሰ/መ/ቁ 73041

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካቾች፡-** ወ/ሮ ሰይዳ ደበሌ - ጠበቃ ዕዮብ ገ/ህይወት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሸሪፍ ሽኩር - በሌሉበት ታይቷል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካችንና ተጠሪን በፍርዱ መሰረት በስምንት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለውን ቤት ተከራካሪዎች የተለያየ ድንበር በማሣያታቸውና ቦታውም ሰነድ አልባ በመሆኑ ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ እንደሆነ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን ጽ/ቤትና ቀበሌው የገለፁት መሆኑን ምክንያት በማድረግ አፈፃፀሙን መቀጠል አይቻልም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች መስከረም 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በጋብቻ ዘመን በጋራ ያፈራነውን ቤት እኩል እንድንካፈል የተሰጠውን ፍርድ ማስፈፀም አስቸጋሪ ነው በሚል ምክንያት አፈፃፀሙ መዘጋቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ መጥሪያ አልቀበልም ስለማለቱ በቃለ መሀላ አረጋግጣ ማመልከቻ አመልካች ስላቀረበች መልስ የመስጠት መብቱን በማለፍ ጉዳዩን በሌለበት መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አፈፃፀም ለመቀጠል አስቸጋሪ ነው የተባለው ቤት አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሀብት መሆኑ ቀደም ሲል ፍርድ ተሰጥቶበታል፡፡ ቦታውና ቤቱ ግብር ሲከፈልበት የኖረ መሆኑንና አመልካችና ተጠሪ ቦታውን ለረዥም ጊዜ ይዘውት እንደነበሩ አመልካች በሥርና በሰበር ካቀረበችው ክርክር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በፍርዱ መሰረት ቦታውና ቤቱን ለማካፈል ወይም በሐራጅ ለመሸጥ አይቻልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የአፈፃፀም መዝገቡን የዘጋው ቦታው ሰነድ አልባ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባልስልጣንና የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር ፅፎልኛል በማለት ነው፡፡

የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378 መሰረት ሲቀርብለት፣ የፍርድ ባለዕዳው የሚያቀርበውን መልስ በመቀበል፣ ፍ/ቤቱ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 386 ተደንግጓል፡፡ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት በመሆኑ እኩል እንዲከፈል፤ እኩል ማካፈል የማይቻል ከሆነ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ውሳኔ የተሰጠበት ንብረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ ይህ ንብረት ካርታ ፕላን ባይኖረውም የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ይዞታ ለመለየት የሚያስችሉ ልዩ ምልክቶችንና የንብረቱን አዋሳኞች በመለየትና ግልፅ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረትና ቦታ ለፍርድ ባለመብትና ለፍርድ ባለዕዳ እኩል እንዲከፍሉ ትዕዛዝ ለመስጠት ወይም እኩል ለማካፈል የማይቻል ከሆነ ቤቱና ቦታው ካርታና ፕላን የሌለው መሆኑንና የንብረቱን አዋሳኞች በጨረታ ማስታወቂያው ላይ በመግለፅ ንብረቱን በመሸጥ ለማካፈል የሚቻልበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 423 ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በፍርድ አፈፃፀም ሂደት እንደዚህ አይነት ችግሮች ሲያጋጥሙት ለፍርዱ አፈፃፀም ተስማሚ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ በፍርድ ቀደም ብሎ የተረጋገጠው ቤት ሰነድ አልባ በመሆኑ ንብረቱን ለማካፈልም ሆነ ለመሸጥ አስቸጋሪ መሆኑን የአስተዳደር አካል ፅፎልኛል በማለት የአፈፃፀም መዝገቡን መዝጋቱ፤ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 371 ንዑስ አንቀጽ 1 የተሰጠውን ፍርድ የማስፈፀም ሥልጣንና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 392 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ሣያርም ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና በማየት ፍርዱን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/392 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመስጠት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

# የዳኝነት
# ሰልጣን